ሐምሌ ፳፮ ፳፻፲፭

August 02/2023

ጉዳዩ፦ የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ United Amhara Political Wing (UAPW) መሠረታዊ መርሆዎች፣ ቁልፍ ዕምነቶች እና ዕቶች፡

የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ በአማራ የፖለቲካ ሱታፌ ዐውድ የነጠረና የራሱን ዐዕማድ ያዋቀረ ሆኖ፣ በአማራ መጻዒ ዕጣ ላይ ለማናቸውም ድርድር የማይቀርብ ርዕዮት እና ፖሊሲዎች አሉት። በብቸኝነትም የአማራ ነገድ (ማኅበረሰብ) ፍላጎትና ማንነት ማጠየቂያ ማንጸሪያ ተቋም ሲሆን፣ የአማራን ሁሉን-አቀፍ ፖለቲካዊ ውክልና፣ የጸና ደህንነት እና የማይገሰሱ መብቶች ባለቤት በማድረግ ሂደት ውስጥ የማይናወጥ አቋም አለው። የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ በጽናት የሚቆምላቸው ቁልፍ ዕሴቶቹም ሕገ-መንግስቱን በመለወጥ፣ ሐሰዊ ትርክትን በመርታት፣ ታሪካዊ ባላንጣዎቸን ከማክሰም፣ የአማራ ማንነትና ብሔርተኝነትን በጽኑ መሠረት ስለማኖር፣ አማራዊ የአገረ-መንግሥት ባለሚልነትን ማስቀጠል፣ ዐጽመ-ርስቶቻችን ደጃፎቻቸውን ማስከበር እና ፋኖ የአማራ መከላከያ መሆኑን በስፋት ማሳወቅ ነው።

<u>ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳይ</u>፡ የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ አሁን በሥራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት እና የክልሎች አመሠራረት፣ አወቃቀርና ሕገ-መንግሥቱ ያደራጀውን አማራ ጠል የጎሳ ሥሪት በፍጹም አይቀበልም፣ ለህገመንግስቱ ዕውቅናም አይሰጥም። በዚህ ህገመንግስት የፀደቁ ሀገራዊና አለማቀፋዊ የአማራውን ህልውናና ሀብት የገፉ ውስኔዎችን እውቅና አይሰጥም። የአማራው ሕዝብና ፖለቲካዊ ርዕዮት ሱታፌ የተረጋገጠበት የአማራን ሁለንተናዊ ጥቅሞቸን የሚጠብቅና የሚያረጋግጥ አዲስ ሕገ-መንግሥት እናዘጋጃለን፣ ሕገ-መንግሥታዊ ሥሪትም እናጸናለን።

<u>ሐሰዊ ትርክት</u>፡ የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ አማራ በኢትዮጵያ ግዛተ-መንግሥት እና ታሪክ ውስጥ አንኳር ድርሻ ማበርከቱን በሸፍጥ በማኮሰስና በሐሳዊ ትርክት በመተካት ሲሳደድና ሲባዝን እንዲኖር ተደርጓል። ይህን የተንሻፈፈ አውዳሚ ትርክት በማክሰም በኢትዮጵያ የታሪክና ሥልጣኔ ማዕድ ተገቢውን ክብርና ተግባራዊ ትሩፋት እንዲጎናጸፍ አድርገን ዳግም እንተክላቸዋለን። በታሪካዊ ሻጥረኞች የተካበውን ሐሳዊ ትርክት ከመቃወም አልፈን የጥላቻ ካምፑን እናፈርሳለን።

<u>ታሪካዊ ባላንጣዎቻቸንን ማክሰም</u>፡ የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ አማራን በጠላትነት፣ በጨቋኝነትና በፊውዳልነት የሚያሳድዱትን ዐጽራረ-አማራ ስብስብ፣ አደረጃጀቶቸና ማናቸውንም ንቅናቄዎች እስከ አስተሳሰባቸው እስከፍጻሜው ይፋለማል። ከሚፋለማቸው ዕልፍ ዐጽራራት ውስጥ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር/ሠራዊት ወይም በእንግሊዝኛው ምኅጻረ ቃል (OLF/OLA/OPDO)፣ ቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ይባል የነበረው ተገጽላ የብልጽግና ፓርቲ (PP)፣ እና የትግራይ ሕዝብ ነጻ አቅጪ ግንባር (ሕወሐት/TPLF)፣ ሌሎች ፀረ አማራ ብሄሮችን በጥቂቱ ይጠቀሳሉ። በኢትዮጵያ የተሳከረ የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ የብልጽግና ፓርቲ የጥፋት ቸቦ ተሸካሚውን ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን/ADP) ኋላም የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሲባል ቆይቶ አሁን የብልጽግና ክንፍ በሆነው ስብስብ ላይ "የአማራው ጠላት" ስለመሆኑ ጽኑ አቋም አለን።

<u>የአማራ ማንነትና ብሔረተኝነት</u>፡ የአማራን ማንነት፣ ብሄርተኝነት፣ ባሕል፣ ቋንቋ፣ ቅርስና ትውፊት በማሳደግና በማስፋፋት ለሕልውናው የሚገዳደሩትን ኃይላት በማሸነፍ በትዕምርታዊ ጎዳና እንጓዛለን። የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ ነባር ገዢ ዕሴቶችን ያበረታታል፣ የመንግሥትን ጠቅላይነትና ጣልቃ-ገብነትን የሚገድብና በሕግና ሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ይሠራል። ፖለቲካዊ ክንፉ አማራ በባሕል፣ በታሪክ ይዞታውና በሕዝብ ቁጥሩ ግዙፉ እንደመሆኑ የመንግሥትን ጠቅላይነትና ጣልቃ-ገብነትን የሚገድብና በሕግና ሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ይሠራል። ፖለቲካዊ ክንፉ አማራ በባሕል፣ በታሪክ ይዞታውና በሕዝብ ቁጥሩ ግዙፉ እንደመሆኑ በአገሩ ፖለቲካዊና የፍትሕ ተቋማት ውስጥ ተገቢውን እና ትልቁን ሥፍራ ዕንዲይዝ አጥብቆ ይሠራል። እራሱን ከመጥፋት ለመከላከል የሚሠራው የአማራ ብሔረተኝነት ከኢትዮጵያ ማዕቀፍ ቀዳማይ ውጥን ሆኖ ይቀጥላል። ለግብ የሚያደርሰንም ብቸኛው ርዬተ-አለም የአማራ ብሄርተኝነት መሆኑን በቋሚነት ያምናል። ፖለቲካዊ ማጠንጠኛችን እና ጉዟችን በአማራነት ጀምሮ በአማራነት ይደመደማል።

<u>ራስ-ገዝነት</u>፡ የፌደራል መንግስት አግላይ ዕሳቤዎችን በማፍረስ፣ በጊዜና ቦታ ጥልቀት ውስጥ ዘልቆ ለትውልዱ ያወረሰውን የአማራ መንግስታዊ ትልሞችና ዕሴቶች በማሳደግ፣ ግዛታዊ አንድነቱን እና ራስ-ገዝ ሚናውን በማላቅ፣ የአማራን ፖለቲካ-ኢኮኖሚ መሪነት ገዢ ትርክት በማድረግ አማራዊ የአገረ-መንግሥት ባለሚልነትን ማስቀጠል ቀዳሚ ግባችን ነው።

<u>ዐጽመ-ርስቶቻችንን ማጽናት</u>፡ በታሪክ፣ በባሕል እና መልክዐ-ምድራዊ ሥሪታቸው የአማራ የሆኑ ግዛቶች የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ ቋሚ ግብ ናቸው። እነዚህንም ርስቶች፣ በውስጣቸው የያዟቸው ሐብቶችና ጸጋዎች ፍትሐዊ የአማራ ቋሚ ትሩፋቶችና የነገ መንገዱ ፍኖት ማቅኛ መሆናቸውን በአጽንዖት እንይዛለን። በታሪክም ከነዚህ ጸጋዎቹ እንዲርቅ፣ እንዲባዝን እና እንዲታረዝ ያደረጉ ትርክቶችንም በማክሰም ይጓዛል።

<u>ነፍጠኛ -የአማራ መከላከያ ዘብ</u>፡ የተደራጀ የትጥቅ ትግል ብቸኛው የአማራ የመጥፋት አደጋ መቀልበሻ እና የታወጀበትን የዘር ማጽዳት ጦርነት የማርከሻ መንገድ እንደሆነ የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ ያምናል። አማራ በኢትዮጵያ አገረ-መንግስት በህዝብ ብዛትነቱ አንደኛውን ስፍራ ስለሚይዝ ቁልፍ የመንግስት ማለትም ሕግ ማውጣት፣ ፍትሕ ማስፈፀም፣ ዋነኛ ኢኮኖማዊ አውታሮችን መምራት፣ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ተቋማቶችን በመቆጣጠር ንዑድ ድርሻ መያዝ አለበት። ይሕ ካልሆነ በአባቶቹ ፍኖትና አገረ-ሰሪነት ጥበብ ተመርቶ በፈቀደውና የእኔ በሚለው ታሪካዊ ግዛቱ የራሱን መንግሥት ይመሠርታል። ከኦሮሙማው አረመኔያዊ አገዛዝጋር በፍፁም አይደራደርም፣ ለኦሮሙማ ሥርዓት አይገዛም፣ ኦሮሙማ ጋር የሚጋራው ቁራሽ ማዕድ አይኖርም፣ የኦሮሚያን ክልልና ለኦሮሙማ ዝንተ-ዓለም ዕውቅና አይሰጥም። በመሆኑም የአማራ ዐንድነት (ዐዕማደ አማራ) ፖለቲካዊ ክንፍ የፋኖን ትግል እና አደረጃጀት በሙሉ ዕምነት ይደግፋል፣ የተለያዩ የአማራ ፋኖ ቡድኖች በአንድ ዐሐድነት አድገው የአማራ መከላከያ ዘብ (Amhara Defense Force – ADF) እንዲመሠረት አበክሮም ይሠራል።

የአማራ ዐንድነት ፖለቲካዊ ክንፍ
ክብር ለተሰውት ፋኖዎች ‼
ድል ለፋኖ ‼
ድል ለአማራ ህዝብ ‼